# <u>ኢህአዴግና የሉዓላዊነት ጉዳይ</u>

ሸዋይልማ ኪዳኔ
ጁን 2008 ዓ.ም (ጀርመን)

*“…በእርግጥ የመለስ ቡድን ኢ-ሃገራዊ አዝማሚያዎች ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊትና በጦርነቱ ሂደት የታዩ ቢሆንም ወደ ከፍተኛ ደረጃ የተሸጋገረውና የአገራችንን ሉዓላዊነት ለኤርትራ አሳልፎ የሚሰጠውን የአልጀርሱን ቴክኒካል አሬንጅመንት ሰነድ ካልተቀበልን ሞቼ እገኛለሁ የሚል አቋም የያዘበት ወቅት ነበር።…”*

ከሕወሓት የተገለሉት የአመራር አባላት
ከእባብ እንቁላል እርግብ አንጠብቅም ብለው ካወጡ ጹሑፍ የተወሰደ ጁላይ 2003 ዓ.ም

*“…ኢህአዴግ ከሱዳን መንግስት ጋር በድንበር ጉዳይ ላይ ውይይት አካሂዶ ድንበር ለማካለል የተንቀሳቀሰ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ መንግስት ነው። …ከኢህአዴግ በፊት የነበሩት መንግስታት በድንበር ጉዳይ ከሱዳን መንግስት ጋር የዚህን ያህል ተጉዘው አያውቁም።…”*

ሚስተር ኦስማን አልሰይድ ፋዲል አልሰይድ የሱዳን አምባሳደር
ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ካደረጉት ቃለ ምልልስ የተወሰደ ኖቬምበር 14 ቀን 2004 ዓ.ም

*“…አንዳንድ ምሁራን ይህንን ረቂቅ ሕግ (ኤች አር 2003) ከውጫያሌው ስምምነት ጋር አያይዘው ነው የሚያዩት። ሁለተኛው የውጫሌው ሕግ ነው እያሉ እየፈጁት ያሉት፣ እያመሳሰሉ ያሉት። እኔ የተሳሳቱ አይመስለኝም። ለምን ? የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመድፈር፣ ኢትዮጵያ በአሜሪካ ኮንግረስ፣ በአሜሪካ እጅ አዙር አስተዳዳሪነት እንድትቀመጥ የሚያደርግ ሕግ ነው።…”*

አቶ ስዩም መስፍን የውጭጉዳይ ሚ/ርና የህወሓት ም/ሊቀመንበር
ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮን ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ኖቨምበር 6 ቀን 2007 ዓ.ም

*“…ድንበሩ ዳግም እንዲካለል ተስማምተናል። በማካለሉ ተግባር ላይ አንድም የሱዳንም ሆነ ኢትዮጵያዊ ገበሬ ከሚያርሰው መሬት እንዳይፈናቀል ተስማምተናል። ኢትዮጵያዊያኖች በሚያርሱት መሬት ላይ እንዲቀትሉ በማያርሱት መሬት ላይ ሱዳንያዊያኖች እንዲያርሱ ተስማምተናል። አንድም የተፈናቀለ ኢትዮጵያዊ የለም። ለወደፊትም የሚፈናቀል አንድም ኢትዮጵያዊ አይኖርም። ከሱዳን ወስደን ለኢንቨስተሮች ሰጥተን የነበረውን መሬት ነው ለሱዳን መንግስት መልሰን የሰጠነው።…”*

ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ
በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለቀረበ ጥያቄ ከሰጡት መልስ የተወሰደ ሜይ 22 ቀን 2008 ዓ.ም

## መግቢያ

ይህን ጹሑፍ ከተቀመጠበት አንስቼ ለብሶት የነበረውን አቧራ አራግፌ መጠነኛ ለውጥ በማድረግ የሚቀነሰውን ቀንሼ መጨመር ይኖርበታል ብዬ ያመንኩባቸውን ነጥቦች አካትቼ ለንባብ እንዳቀርበው ያስገደደኝ ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ያለውን 1600 ኪሎ ሜትር የድንበር መሬት ኢህአዴግ ለሱዳን መንግስት ሊያስረክብ መዘጋጀቱን የሚገልጸው ዜና በኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ኮሚቴ አማካኝነት መሰራጨት በመጀመሩ ነው። በመሆኑም የጹሑፉ ዋነኛ ዓላማ ኢህአዴግ ስለ ሉዓላዊነት ነጋ ጠባ በሚያወራው ቃልና ተግባር መሃከል ያለውን ልዩነት መዳሰስ ይሆናል። በእርግጥ ኢህአዴግና ደጋፊዎቼ ኤች አር 2003 በኢትዮጵያ የዲሞክራሲና የተጠያቂነት ረቂቅ ሕግን (HR 2003: Ethiopia Democracy and Accountability Act of 2003) ከውጫሌው ውል ጋር በማወዳደር ረቂቅ ሕጉን ሲደግፉ የነበሩ ኢትዮጵያዊያኖችን በከሀዲነት እስከ መክሰስ ደርሰው ስለነበር የውጫሌውን ስምምነትና ረቂቅ ሕጉን በመጠኑም ቢሆን መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 8 ቁጥር 1 ላይ ሉዓላዊነትን በተመለከተ: "የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ናቸው" ይላል። እንግዲህ ከሕገ መንግስቱ እንዳምንረዳው የሉዓላዊነት ጉዳይ ለገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ብቻ የተሰጠ መብት ሳይሆን ሁሉንም ዜጋ በእኩልነት የሚመለከት የማንነት ጉዳይ ነው ማለት ነው። ሉዓላዊነት አገርን፣ መንግስትንና የዜጎችን መብት የሚያጠቃልል ጉዳይ ነው። ሉዓላዊነታችን ተደፈረ ስንል አገራችን ኢትዮጵያ፣ የመንግስትና የዜጎች መብቶች በሌላ ባዕድ በሆነ አገርና መንግስት ተደፈረ ማለት ነው። በአጭሩ በሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ በዜጎችና በመንግስት፣ በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መሀከል ልዩነት ሊኖር አይችልም። ለምሳሌ ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በደፈረበት ወቅት በአገር ውስጥና በውጭ በሚኖረው ሕዝቡ ዘንድ ታይቶ የነበረውን አንድነትና ትብብር የሚዘነጋ ያለ አይመስለኝም። ኢህአዴግን እንደዚያ ጊዜ ከሕዝብ ጋር ያቀራረበ አጋጣሚ ያለ አይመስለኝም። የሉዓላዊነትን ጉዳይ ለውስጥ የፖለቲካ ክስረት እንደ የፖለቲካ መሳሪያነት ሲጠቀሙበት ግን በዜጎችና በመንግስት፣ በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚ ድርጅቶች መሃከል ልዮነት ይፈጠራል። ጠ/ሚር መለስ ዜናዊ በሱማሊያ ላይ የውክልና ጦርነት (Proxy War) ለማወጅ የተወካዮች ም/ቤትን ፈቃድ ሲጠይቁ የሕዝብ ተወካዮች በሆኑ የተቃዋሚ ድርጅት አባላት የገጠማቸውን ተቃውሞ አይተናል። በከተማውም ህዝብ ዘንድ ይህ የውክልና ጦርነት የመለስ ዜናዊ ጦርነት ተብሎ እስከመጠራት ደርሷል። የኢትዮጵያ ጦር ባድመን ሲያስለቅቅ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ያለምንም ጥሪ አደባባይ ወጥቶ በደስታ ጨፍሮ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ሞቃዲሾን ከተማን ሲቆጣጠር ግን ደስታውን ለመግለጽ አድባባይ የወጣ አንድ ሰው አልነበረም። ለምን ?! እንግዲህ በዜጎችና በመንግስት መሓከል በሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ ልዩነት ሲፋጠር ችግር አለ ማለት ነው።

## ብድርና ዕርዳታ

እንደ ኢትዮጵያ ባለ ድሃ አገር ውስጥ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ብድርና እርዳታ የራሱ በጎ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንዳለው የሚካድ አይደለም። የኢትዮጵያ መንግስት በጀትም 40 በመቶው በውጭ እርዳታና ብድር የሚሸፈን መሆኑ የሚታወቅ ነው። ዛሬ በአገራችን ውስጥ በአይን የሚታዩ የተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ከውጭ በእርዳታና በብድር በተገኘ ገንዘብ እንጂ መንግስት በአገር ውስጥ በሚሰበስበው ግብርና ቀረጥ የሚሰሩ ስራዎች አይደሉም፣ ሊሰሩም አይችሉም። ልማት የአንድ አገር ሕዝብ ህይወቱን አዎንታዊ በሆነ መንገድ ለመለወጥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ውጤት ነው። እንግዲህ ብድርና እርዳታ በተገቢው ቦታ ላይ የሚውል ከሆነ የሕዝቡ ታታሪነትና ተሳትፎ ታክሎበት ልማትን ለማፋጠን ይረዳል። የአፄ ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻው የስልጣን ሰዓት ላይ ኢትዮጵያ የነበረባት የውጭ ዕዳ 371 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን የሃገሪቱ ዓመታዊ ምርት (GDP) 14 በመቶ እንደነበር ይነገራል። በደርግ ስርዓት የውጭ ዕዳው ወደ 8.8 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነበር። ያውም 78 በመቶ የሚሆነው ከሶቪየት ህብረት የተገኘ ነበር። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ከሁለት ዓመት በኋላ የአገሪቱ ዕዳ ወደ 10 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሶ ነበር። የሶቪየት ህብረት ብድር በፓሪስ ክለብ ጫና ከተቀነሰ በኋላ አሁን ኢትዮጵያ ያለባት ዕዳ ወደ 5.5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው።

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ በኋላ ከበለጽጉ አገሮች ለታዳጊ አገሮች የሚሰጡ የልማት ዕርዳታዎች የመመዘኛ መስፈርቶች (Criteria) አሏቸው። ለምሳሌ የጀርመን መንግስት ለልማት እርዳታ እንደዋነኛ መስፈርት ከሚያያቸው ጉዳዮች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕዝብ ተሳትፎ፣ የሕግ የበላይነት፣ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መኖርና የመንግስት ሚና በልማት እንቅስቃሴ ላይ በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው። ኤች አር 2003 ረቂቅ ሕግም ለነዚህ ጉዳዮች ነው ትኩረት የሚሰጠው። እነዚህ ሁኔታዎ ተሟልተው በማይገኙበት አገር ውስጥ ዜጎች ለፍትህና ለዲሞክራሲዊ ሥርዓት ትግል የሚያደርጉ ከሆነ ለጋሽ አገሮች የልማት ዕርዳታውን የሕዝቡን ትግል ለመደገፍ እንደ መሳሪያ በመጠቀም በመንግስቱ ላይ

ጫናና ተጽዕኖ ያደርጋሉ። እንደዚህ ዓይነቱ ተጽዕኖ ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም በመሆኑ በጫናው እንቅልፍ የሚያጣው መንግስት ብቻ ይሆናል። ኤች አር 2003 ረቂቅ ሕግ በጣም ያስቆጣውና ያንገበገው ገዢውን ፓርቲ ኢህአዴግን እንጂ ሕዝቡን አልነበረም።

በኢትዮጵያ ውስጥ የልማት ዕድገት እንዳይኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው አይመስለኝም። ሆኖም ግን የሰው ልጅ ከልማትም በላይ ስብዕናው እንዲከበርለት ይፈልጋል። ልማት ከቁሳዊ ምርት ባሻገር የመብት ጉዳዮችም አሉት። የሰው ልጅ በዳቦ ብቻ አይኖርም የሚለው አባባል የልማት ፅንሰ ሓሳብ መሆኑን የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለአገራችን የልማት ጉዞ ዋና እንቅፋት የሆነው የኢህአዴግ የፖለቲካ አካሄድ ማለትም ከተቃዋሚዎቹ ጋር አብሮ ለመስራት የፖለቲካ ፍላጎትና መቻቻል ያለመኖር ብቻ ነው። እንግዲህ ብድርና እርዳታ ጠቃሚ መሆኑን የተስማማንበት ጉዳይ ይመስለኛል። ሆኖም ግን ለብድርና ዕርዳታ ሲባል ብቻ የአገር ሉዓላዊነት ለድርድር አይቀርብም። ኢህአዴግ ግን ይህን አድርጓል። ይህን የሚሉን የኢህአዴግ አባላትና የመንግስት ከፍተኛ ባልስልጣናት የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃና አቶ ገብሩ አስራት ናቸው። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የኢህአዴግ መንግስት በተለይም ጠ/ሚሩ የሄጉን ውሳኔ ካልተቀበል የውጭ ድብርና እርዳታ አናገኝም። የውጭ ብድርና እርዳታ ካላገኘን ደግሞ ድህነትን መቅረፍና ዕድገት ማምጣት አንችልም፣ ለድርቅ የጠየቅነውንም የእህል ዕርዳታ ልናጣ እንችላለን። በዚህም ሳቢያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የተራቡ ዜጎቻችን ሊያልቁ ይችላሉ በማለት የሉዓላዊነት ጉዳይ ለድርድር እንዲቀርብ ተደርጓል። እንግዲህ የኢህአዴግ መንግስት በአንድ በኩል ሉዓላዊነታችንን እናስከብራለን ይለናል። በሌላ በኩል ደግሞ ከሉዓላዊነታችን በላይ ፋይዳ ያላቸው አገራዊ ዓላማዎች አሉን፣ ድህነትን ለመዋጋት ድህነት ላይ ጦርነት ከፍተናል፣ ድህነትን ጨርሶ ለማጥፋት በሚደረገው ጦርነት ሁሉም ይሰለፍ፣ ልማታችንን ለማፋጠን፣ ለሰላምና የመልካም አስተዳደር ግንባታችን ስንል የምንከፍለው መስዕዋትናት መኖሩን መርሳት የለብንም ይል ነበር። ድህነትን መዋጋትና ሉዓላዊነትን ማሰጠበቅ ግን ተፃራሪ የሆኑ ጉዳዮች አይደሉም ሲልም ነበር። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በራሱ በህወሓት አመራር ውስጥ በሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ አለመግባባት ተፈጥሮ ለመከፋፈል ምክኒያት እስከመሆን ደርሷል። የቀድሞ የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ገብሩ አስራት የመሰረቱ የፖለቲካ ፓርቲ አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና **ሉዓላዊነት** ፓርቲ ተብሎ ይጠራል። በፓርቲው መጠሪያ ላይ **ሉዓላዊነት** የሚለው ቃል የፓርቲው መጠሪያ ስም ውስጥ መግባቱ ኢህአዴግ ለዚህች አገር ሉዓላዊነት የሚቆረቆር መንግስት አይደለም የሚል አንደምታ ያለው ይመስለኛል። ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊንም ሆነ ሌሎችን ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ከአቶ አስራት ገብሩና ከአቶ ስዬ አብርሃ በላይ ጠንቅቆ የሚያቅ ሰው ያለ አይመስለኝም።

## የውጫሌው ውል

የአጼ ዮሓንስ በመተማ ላይ መውደቀ ዜና በኢጣሊያኖች ዘንድ ከፍተኛ የደስታ ስሜት ፈጠሮ ነበር። የደስታቸው ስሜት መንስዔው በኤርትራ ጉዳይ ላይ ከአሁን በኃላ ከእኛ ጋር ጦርነት መግጠም የሚፈልግ ስለማይኖር ከጊንዳ አስመራ፣ ከአስመራ መረብን አልፈን ለኢጣሊያን አዲስና ሰፊ የቅኝ ግዛት እንፈጥራለን ከሚል ስሜት የመነጨ ነበር። በአጼ ምኒሊክ መንግስት ዘንድ የጣሊያን መንግስት ተወካይ የነበረው ኮንት ፒዮትሮ አንቶኔሊ ጣሊያን ከንጉስ ምኒሊክ ጋር ያላትን የወዳጅነት ግንኙነት አጠንክራ ንጉሱ የሚፈቅዱትን መሬት ይዞ በሰላም መቆየት ይሻላል የሚል አመለካከት ስለነበረው ምጥዋ ከነበረው የጣሊያን የጦር አለቆች ጋር የማይጣጣም አቋም ነበረው። በሮም የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ከአዲስ አበባና ከምጥዋ የሚመጡትን በይዘት የተለያዩ የቴሌግራም መልዕክቶች በጥሞና እያነበቡና እያጤኑ መካከለኛ ውሳኔ በመውሰድ ይጠቀሙ ነበር። የኢጣሊያን ጦር ከጊንዳ ተነስቶ ወደ አስመራ የገባው አጼ ዮሓንስ ከሞቱ በኃላ በአገር ወስጥ ሆዳሞች ታጅቦ ነበር። ጣሊያን አስመራን እንደተቆጣጠረች የወሰኗን ፀጥታ ለመጠበቅ መንቀሳቀስ ጀመረች።

የጣሊያኑ ተወካይ ኮንት አንቶኔሊ ንጉስ ምኒሊክን እየመከረና እያግባባ ለኢጣሊያን ንጉስ ለኡምቤርቶ ደብዳቤ እዲጽፉና የትግሬ ሹማምንቶችን በምጥዋ በኩል መሳሪያ እያስገቡ እንዳይወጓቸው በአስመራ ያሉ ሹማምንቶቾን ይጠይቁልኝ ብለው እንዲማጸኑ አድርጓቸው ነበር። ዋናው የአጼ ምኒሊክ ሃሳብ ግን የጦር መሳሪያን ጥቅሙንና ጉዳቱን በጣም ለይተው ስለሚያውቁ ራስ መንገሻም፣ ሌላውም ዙፋን ተቀናቃኝ በምጥዋ በኩል መሳሪያ እንዳያገኝ ለማድረግ ነበር። የጣሊያኑ ተወካይ ጥረት ደግሞ ንጉስ ምኒሊክን በተዘዋዋሪ የጣሊያንን በአስመራና በተያዙ ወረዳዎች ውስጥ ያላትን የቅኝ ግዛት ባለቤትነት እንዲቀበሉ ለማድረግ ነበር። የጣሊያኑ ተወካይ የጣሊያን መንግስት ለአጼ ምኒሊክ ፍፁም ወዳጅ በመሆኑ የብድር ገንዘብና የጦር መሳሪያ፣ የንግድና የወዳጅነት ግንኙነት ለመፍጠር በይፋ አንድ ስምምነት በመፈረምና የኢትዮጵያም ዋና መልዕክተኛ ሮማ ሄዶ ከኢጣሊያን ንጉስ ከኡምቤርቶ ጋር ሲገናኝ እንደሆነ ጠቅሶ ከሮማ የተላከለትን የውል ረቂቅ ንጉስ ምኒሊክ ውጫሌ ላይ በሰፈሩበት ጊዜ አቅርቦ ትንሽ ምክር ተካሂዶበት አጼ ምኒሊክና የጣሊያኑ ተወካይ አንቶኔሊ የጣሊያን ንጉስን ወክሎ

ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም የውጫሌን ውል ተዋዋሉ።እንግዲህ የሜይ 2 ቀን 1889 ዓ.ም እና የእሱ ተቀጥላ የሆነው የኦክቶበር 1 ቀን 1889 ዓ.ም ስምምነት ነው የውጫሌ ስምምነት በመባል የሚታወቀው።

የውጫሌ ውል በኢትዮጵያና በኢጣሊያን ንጉሰ ነገሥታት መካከል የተካሄደ ውል ነው። ውሉ 20 አንቀጾች አሉት። የውጫሌ ስምምነት ኢትዮጵያ በጣሊያን የተያዘውን የሰሜን ግዛቷ ባህረ ነጋሽን (ኤርትራ) ለጣሊያን ቅኝ ግዛት እውቅና የሚሰጥ ስምምነት ነው። የውጫሌ ውል ውስጥ አንቀጽ 17 በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ከወሰኑ የበለጠ ጠብ ቀሰቀሰ። አንቀጽ 17 : "የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት ከአውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በጣሊያን አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል።" ይላል። የዚህ አንቀጽ መንፈስ ኢትዮጵያን በጣሊያን ጠባቂነት ውስጥ እንድትሆን የሚያደርግ ነበር። ይህ እንግዲህ ንጉስ ምኒሊክም በኢጣሊያን ንጉስ አማካኝነት ካልሆነ በቀር ከማንም የአውሮፓ መንግስት መሪ ጋር ሊደራደሩና ሊዋዋሉ አይችሉም የሚል ነበር። ይህን አንቀጽ ንጉስ ምኒልክ ያልወደዱት ቢሆንም በጣሊያኑ ተወካይ በኩል ይህ አንቀጽ በዚህ ውል ውስጥ ከሌለ የኢትዮጵያ ጥቅም ሲነካ ጣሊያን አፏን ሞልታ ለመቃወም አትችልም በሚል የወዳጅነት ሽፋን ስም አንቀጹ እናዳይሰረዝ ማድረግ ችሏል። ንጉስ ምኒልክ ግን ባንድ በኩል የውጭ ተጽዕኖና ወረራ በሰሜንና በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚያንዣብበት ወቅት ስለነበር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአጼ ዮሓንስ ሞት ምክኒያት መሳፍንቶች የራሳቸውን ግዛት አደላድለው ለመያዝ የሚሯሯጡበት ወቅት ስለነበር የሁኔታዎቹ አስቸጋሪነት አስገድዷቸው እያቅማሙና እያንገራገሩ ነው የውጫሌ ውልን የፈረሙት።

ንጉስ ምኒሊክ ማርች 2 ቀን 1896 ዓ.ም አድዋ ላይ የጣሊያን ሰራዊትን ድል አደረጉ። ከጦርነቱ በኃላ ኦክቶበር 26 ቀን1896 ዓ.ም ከጣሊያን ጋር ሌላ ስምምነት አደረጉ። ይህ ስምምነት የውጫሌ ስምምነትን የሚሰርዝ ነው። ስምምነቱ ከአድዋ ጦርነት በፊት የነበረውን እንዳለ የሚተው ቢሆንም ድንበር እስከሚካለል ድረስ መረብ፣ በለሳና ሙና የተባሉትን ሶስት ወንዞች በኢትዮጵያና በጣሊያን ቅኝ ገዢ መሃከል እንደ ጊዚያዊ ድንበር እንዲያገለግሉ እውቅና የሚሰጥ ነው። የጁላይ 10 ቀን 1990 ዓ.ም ስምምነት ደግሞ የኦክቶበር 26 ቀን 1896 ዓ.ም ስምምነት የሚሰርዝ ነው። እዚህ ላይ ከላይ የተጠቀሱት ሶስት ወንዞች አዋሳኝነት ተሰርዟል ማለት ነው። ሆኖም ግን ሁለቱም 1896 ዓ.ም እና 1900 ዓ.ም ስምምነቶች በማያሻማ መልኩ ኤርትራን በምንም ዓይነት ለሌላ አሳልፎ መስጠት ወይም መሸጥ እንደማይቻል ጣሊያን የተስማማባቸው ውሎች ናቸው። የ1900 ዓ.ም ስምምነት ላይ ሁለት ስምምነት ሳይሆን እንደ ተጨማሪ ማስታዎሻዎች (Notes) ሊታዩ የሚችሉ 1902 ዓ.ም እና 1908 ዓ.ም በኢትዮጵያና በጣሊያን ቅኝ መሃከል ያለውን የምዕራቡንና የምስራቁን ድንበር የሚመለከቱ ተጨማሪ ውሎች ተጨምረዋል። ሆኖም ግን እነዚህ ስምምነቶች እስከ 1908 ዓ.ም ድረስ አሰብና አካባቢውን ያልጨመረ ስምምነት ነበር። ጣሊያን በስምምነቱ የተካተቱትን ቦታዎች በሙሉ እንኳን ሊያስተዳድር ቀርቶ በመጨረሻ በኢትዮጵያ ተሸንፎ እስከተባረረበት ጊዜ ድረስ ለአንድ ቀን እንኳን በእግሩ ያልረገጣቸው ሆኖም ግን በስምምነቱ የተካተቱ አካባቢዎች ብዙ ናቸው። አጼ ምኒሊክ የውጫሌን ውል ሕሊናቸው ፈቅዶና ሙሉ እምነት አድሮባቸው የፈረሙት ውል ስላልነበር መጨረሻ ላይ ውሉን መሰረዛቸውንና እንዲያውም የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ከምጥዋ አልፎ ሕንድ ውቅያኖስ መድረሱን አሳወቁ።

## የአልጀርስ ስምምነት

ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በፊት የወያኔና የሻዕቢያ ግንኙነት ቅጥ ያጣና ቃል ሊገኝለት የማይችል ግንኙነት ነበር። የኤርትራና የኢትዮጵያ የማዕድን ባለሙያዎች ትብብር ሃሳብ ለመለዋወጥ የሚያስችል ስብሰባ አክሱም ውስጥ ከጦርነቱ በፊት ተካሂዶ ነበር። በዚህ ስብሰባ የወያኔ የንግድ ድርጅቶች ስብስብ የሆነው ትእምት (EFORT) ውስጥ የሚሰሩ የማዕድን ባለሙያዎች ኢትዮጵያን ውክለው ቀረቡ። በስብሰባው የኤርትራ ማዕድን ባለሙያዎች ብዙ ስራ አልሰራንም፣ ልምድም የለንምና ለዛሬው የምናቀርበው ምንም ነገር የለም ብለው ቁጭ አሉ። የኤፈርት የማዕድን ባለሙያዎች ግን በአካባቢው ያሉ የማዕድን ቦታዎችን እየዘረዘሩ አቀረቡ። በባድመ በኩል ያለው የማዕድን ክምችት በሚገባ ገልጸው የጥናቱን ሰነድ ሳይቀር ለኤርትራዊያን ሰጡ። የኢህአዴግ መንግስት ከሻዕቢያ ጋር ፍቅር ላይ በነበረበት ወቅት ሌላው ቀርቶ ለማንም የማይሰጥ የአየር ኃይል የኮምፒውተር ዳታቤዝ (Database) ለሻዕቢያ በትብብር ሽፋን ስም በመስጠት፣ የደህንነት ተቋም ጭምር ሳይቀር ለሻዕቢያ ክፍት ተደርጎ ስለነበር ሻዕቢያ ከኢትዮጵያ የጦር አዛዦች በላይ የተሟላ መረጃ የነበረው እንደነበር በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነበር። ሻዕቢያ ግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ.ም ኢትዮጵያን ሲወር ባድመን ጨምሮ በዚያ ጥናት ውስጥ የተካተቱ አካባቢዎችን ነበር የተቆጣጠረው።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አአድ) ከጁን 8 እስከ 10 ቀን 1998 ዓ.ም ቡርኪናፋሶ ውስጥ ባካሄደው 34ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የተፈጠረውን የድንበር ጭቅጭቅ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ሰነድ (OAU Framework Agreement for a peaceful

Settelment of the Dispute between Ethiopia and Eritrea) ለሁለቱ መንግስታት አቀረበ። ቀጥሎም አልጀርስ ላይ ከጁላይ 12 እስከ 14 ቀን 1999 ዓ.ም በተካሄደው የአአድ 35ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ ቡርኪናፋሶ ላይ ቀርቦ የነበረውን የሰላም ሃሳብ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ቴክኒካል አሬንጅመንት ሰነድ (Technical Arrangement for Implimentation of the OAU Framework Agreement and ist Modalities) ተዘጋጅቶ ውሳኔ እንዲሰጡበት ለሁለቱ መንግስታት ቀረበ። ሰነዱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ማዕከላዊ ኮሚቴዎች በየራሳቸው መድረኮች ለየብቻ ተወያይተው ውስኔ ከሰጡበት በኃላ በኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ም/ቤት ቀርቦ ውሳኔ ተሰጥቶበታል። የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት (ሕዝቡ) ሰነዱን እንዲያውቀውና እንዲወያይበት እድል አልተሰጠውም። ይህ ሰነድ በኢህአዴግ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ለውይይት በቀረበበት ጊዜ የከረሩ ክርክሮች መካሄድ ጀመሩ። ለእነዚህ የከረሩ ክርክሮች ምክኒያት የሆነው የአገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ለህወሓት መከፋፈል ምክኒያት ሆነ። ህወሓት ውስጥ ከጥር 1 ቀን ጀምሮ ሳይቋረጥ እስከ የካቲት 21 ቀን 1993 ዓ.ም በተካሄደው የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ በተለያዩ ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ መክሮ በተለይም አደጋችን ተንበርካኪነት ነው ወይስ ቦናፓርቲዝም (የአቅጣጫ) ነው በሚለው ነጥብ ላይ ብቻ ውይይት ተካሂዶ የካቲት 21 ቀን 1993 ዓ.ም አደጋው ቦናፓርቲዝም ነው የሚለው የአቶ መለስ ቡድን 15ለ13 በሆነ ጠባብ የድምጽ ብልጫ የእነ ስዬ አብርሃን ቡድን ካሸነፈ በኃላ የወያኔ አመራር ለሁለት ተከፈለ። የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም 12ቱ የወያኔ ከፍተኛ የአመራር አባላት ከድርጅቱ መባረራቸውን የሚገልጽ ደብደቤ ተሰራጨ። በጣም የሚገርመው 12ቱ የህወሓት የአመረር አባላት መታገዳቸውን የሚገልጸው ደብዳቤ የተጻፈው በድርጅቱ በህወሓት ሳይሆን በጠ/ሚኒስትሩ በአቶ መለስ ጽ/ቤት ማህተም ነበር።

ኢትዮጵያና ኤርትራ በአአድ 35ኛው መደበኛ ጉባኤ ላይ ቀርቦ የነበረውን ሰነድ መቀበላቸውን በማረጋገጥ በመሃከላቸው ያለውን ጥላቻ አቁመው በሰላማዊ መንገድ ችግራቸውን ለመፍታት ተስማምተው ጁን 18 ቀን 2000 ዓ.ም የአልጀርሱን ስምምነት ተፈራረሙ። ስምምነቱ ስድስት አንቀጾች አሉት። የአልጀርሱን ስምምነት በጣም ልዩ የሚያደርገው ከዚህ በፊት በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በጦርነት አሸናፊና ተሸናፊ በእኩል እንዲያውም ተሸናፊውን በሚጠቅም መልኩ የተፈጸመ ስምምነት መሆኑ ነበር። የአልጀርሱ ስምምነት አንቀጽ 4.2 የኢትዮጵያና የኤርትራን ድንበር ለማካለል 1900 , 1902 እና 1908 ዓ.ም የኮለኒ ስምምነቶችና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ስምምነቶችን መሰረት ያደርጋል ይላል። እነዚህን የኮለኒ ስምምነቶች ከላይ የውጫሌ ውል ላይ በመጠኑም ቢሆን ተጠቅሰዋል። የጁላይ 10 ቀን 1990 ዓ.ም ስምምነት የሚመለከተው የበለሳ ሙና የድንበር ክልልን ነው። የ1902 ዓ.ም የሰሜን ምዕራብ፣ የሜይ 16 ቀን 1908 ዓ.ም ውል ደግሞ የስሜን ምስራቅ ድንበርን ያካልላል። የ1902 እና 1908 ስምምነቶች በጣሊያንም ሆነ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል በተግባር ያልተከናወኑ በወረቀት ላይ ብቻ ሰፍረው የቀሩ ስምምነቶች ናቸው። የጣሊያን ወረራ በጣሊያንና በኢትዮጵያ መንግስታት መሃከል የተካሄዱትን ስምምነቶች በሙሉ ውድቅ ያደርጋል። በተጨማሪም 1947 ዓ.ም ስምምነት ጣሊያን በኤርትራ ላይ ያለውን የግዛት መብት በገዛ ፈቃዱ ውድቅ የሚያደርግ ነው። ስለሆነም ያስልጀርሱ ስምምነት አንቀጽ 4.2 በሁለቱ አገሮች መሃከል ድንበር ለማካለል መሰረት ያደረጋቸው የቅኝ ግዛት ውሎች የሞቱና የተቀበሩ ስምምነቶች ናቸው። በመንግስታት ታሪክ ውስጥ የሞተን ስምምነት አንስቶ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ ጥቅምና ደህንነት በሚጎዳ መልኩ ተግባራዊ ያደረገ መንግስት ቢኖር የኢህአዴግ መንግስት ብቻ ነው።

የድንበር ኮምሽኑ በ2001 ዓ.ም ተመሰረተ። ኮምሽኑ ውሳኔውን አፕሪል 13 ቀን 2002 ዓ.ም ይፋ አደረገ። በስምምነቱ መሰረት የሄግ ፍርድ ቤት ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የሌለው እንደሆነ ተደንግጓል። የኮምሽኑ ውሳኔ በተሰጠበት ዕለት ሚያዚያ 5 ቀን 1994 ዓ.ም ከሚኒስትሮች ም/ቤት የተሰጠው መግለጫ የድንበር ኮምሽኑ ውሳኔ ህጋዊ የፍርድ ቤት ውሳኔ በመሆኑ ይዘቱም በመሰረቱ ፍትሃዊ በመሆኑ በውሳኔውም መሰረት ባድመ ለኢትዮጵያ መሰጠቷን ጠቅሶ የኢፌዴሪ መንግስት በአልጀርሱ ስምምነት መሰረት ውሳኔውን ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ገለጸ። በተጨማሪም በዕለቱ የውጭ ጉዳይ ሚ/ሩ አቶ ስዩም መስፍን በጦርነቱም በሰላሙም መንገድ ማሸነፋችንና ባድሜም ለኢትዮጵያ መሰጠቷን በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ተናግረው የኢትዮጵያን ሕዝብ በደስታ በአየር ላይ እንዲሳፈፍና እንዲፈነድቅ አደረጉት። በኮምሽኑ ውሳኔ መሰረት ግን ባድሜ ለኤርትራ በመሰጠቱ በኢህአዴግ መንግስትና በሕዝቡ መሃከል በሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ ልዩነት በመፈጠሩና በተለይም ሠራዊቱ የሕዝቡን ስሜት የሚጋራ መሆኑ ምልክቶች በመታየታቸ የኢህአዴግ መንግስት የሄጉን የፍርድ ቤት ውሳኔ ላለመቀበል ምክንያት በመደርደር ከውሳኔው ማፈግፈግ ጀመረ ። በመስከረም ወር 1996 ዓ.ም ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ የድንበር ኮምሽኑን ውሳኔ በተመለከተ የተቃውሞ ደብዳቤ ለተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ም/ቤት በኢትዮጵያና በኤርትራ የተባበሩት መንግስታት ልዑክ (አንሚ) በኩል ላኩ። የአቶ መለስ ተቃውሞ የዲሴምበር 12 ቀን 2000ዓ.ም የአልጀርሱን ስምምነት አንቀጽ 4.15 የሚጥስ ነው። አንቀጹ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የሌለው መሆኑን ይገልጻል። የሄጉ ፍርድ ቤት የወሰነውን የኢህአዴግ መንግስት ባለመቀበሉ የአልጀርሱ ስምምነት ልክ እንደ ውጫሌው ውል አፋችንን ሞልተን ሞቷል ልንል እንችላለን።

## ኤች አር 2003

ዚምባቡዌ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊና የፖለቲካ መብቶች የሚጣሱባትና በአገሪቱ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ ለሚሹ ዜጎች የማትመች ሀገር መሆንዋን ሌት ተቀን የምንሰማው ዜና ከሆነ ሰንብትዋል። የመገናኛ ብዙሃን፣ የፖሊስ፣ የደህንነትና የሰራዊቱ ኃይል በፕሬዚዳንት ሙጋቤ ሙሉ ቁጥጥር ስር በመሆኑ ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት የማይችሉ ሆነዋል። ፍርድ ቤቶች ነፃ አይደሉም። ተቃዋሚ ድርጅቶች ከፍተኛ ጭና ቢኖርባቸውም የሚቻላቸውን ከማድረግ ግን አልተቆጠቡም። ሕዝቡ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየና መከራውን እያየ ይገኛል። የአሜሪካ መንግስት ዚምባቡዌን በተመለከተ የዚምባቡዌ የዲሞክራሲና የኢኮኖሚ መልሶ ማቋቋም ሕግ / Zimbabwe Democracy and Economic Recovery Act / አውጥቷል። ፕሬዚዳንት ሙጋቤ የአሜሪካ መንግስት ማዕቀብ /Sanction/ ጣለብኝ አሉ እንጂ የዚምባቡዌ ሉዓላዊነት ተደፈረ አላሉም። ወይም ደግሞ በራሳቸው ቅጥር ስር የሚገኙ የአገሪቱን ምሁራን ተሰብስባችሁ ስለ ሉዓላዊነት ቲያትር ስሩልኝ እስከማለት አልደረሱም። የአሜሪካ ኮንግረስ ኤች አር 2003 በኢትዮጵያ የዲሞክራሲና የተጠያቂነት ረቂቅ ሕግ / Ethiopia Democracy and Accountability Act of 2007 / ሕግ እንዲሆንለት ወደ ሴኔት ያሳለፈ ሰሞን የኢህአዴግ ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚደፍርና ኢትዮጵያን በአሜሪካ ኮንግረስ እጅ አዙር አስተዳደር የሚያስገባ ረቂቅ ሕግ እንደሆነ እስኪሰለች ድረስ ይናገሩ ነበር። ኢትዮጵያም በሕገ መንግስት የምትተዳደር በመሆንዋ የተወካዮች ም/ቤት ከሚያወጣው ሕግ ውጭ ኢትዮጵያን የሚያስተዳድር ሕግ ሊኖር አይችልም ብለውም ተናገሩ።

የኢህአዴግ መንግስት የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት (መልካም አስተዳደር) ግንባታን ተግባራዊ ለማድረግ ትኩረት ሰጥተን እየተንቀሳቀስን ነው የሚለው መፈክሩ ሌት ተቀን የሚሰማ በተግባር ግን ችግር ውስጥ ያለ እንቅስቃሴ ነው። የአገራችን ፖለቲካ አግላይና ተገላይ ያለበት ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ነው። በእርግጥ በአዲስ አበባና አንዳንድ የአገሪቱ ከተሞች ውስጥ ቁምጣ ለብሶ ጠመንጃ ይዞ የሚሮጥ ስላላየን ወይም የተኩስ ድምፅ ስላልሰማን ብቻ ሰላም አለ ማለት አይቻልም። በአገሪቱ ውስጥ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ የተቃዋሚ ኃይሎች አሉ። የሚካድ አይደለም። ይልቁንስ የሚበጀው ለምን ብሎ መጠየቁ ይመስለኛል። ለኢህአዴግና ለደጋፊዎቹ ሰላም ማለት ጠንከራ ተቀናቃኞችን አጥፍቶ ወይም መንቀሳቀስ እንዳይችሉ በማድረግ ጠንካራ ተፎካካሪ የሌለበት ሁኔታን መፍጠር አድርገው ብቻ ያዩታል።በአንድ አገር ውስጥ ሰላም ሰፍኗል ለማለት ከሚያስችሉን ጉዳዮች ውስጥ የአመጽና የሽብር ያለመኖር፣ የፖለቲካ መቻቻልና ድርድር መኖርና ከሁሉም በላይ በአእምሮውና በልቡ ውስጥ ሰላም ሰፍኖ፣ ሳይፈራ ከቤቱ ወጥቶ ወደቤቱ መመለስ የሚችል ዜጋ የሚኖርበት ማኅበረሰብ መፍጠር ሲቻልና ሲኖር ነው። በዚህ አይን ካየነው እኛ አገር ውስጥ የሰላም ጅምሩም መኖሩ ያጠራጥራል። ስለ አገራችን ኢኮኖሚ በትክክል ለመናገር የሚያስችል መረጃ ማግኘት ፈጽሞ የማይቻል መሆኑን ኢትዮጵያዊያን ኢኮኖሚስቶች / የመንግስት ቅጥረኛ ያልሆኑ / ደጋግመው የሚናገሩትና የምንሰማው ጉዳይ ነው። በእርግጥ ልክ እንደ ኢህአዴግ መንግስት ደርግም ኢኮኖሚያችን በጣም እያደገ ነው ይል ነበር። የኢኮኖሚ ዕድገት የአንድ መንግስት ጥሩነትና መጥፎነት ከሚለካበት መመዘኛዎች ውስጥ አንዱ ነው። የኢኮኖሚ ዕድገት ደግሞ በአንድ አገር ብሔራዊ ምርት /GDP/ የሚገለጽ ነው። አጠቃላይ ብሔራዊ ምርት ለሕዝብ ቁጥር ሲካፈል የነፍስ ወከፍ ገቢ /per capita Income/ ካደገ፣ ዕድገት አለ ይባላል። በአገራችን ከሀያ ዓመት በፊት 190 የአሜሪካ ዶላር የነበረው የነፍስ ወከፍ ገቢ በአሁኑ ጊዜ ከ100 የአሜሪካ ዶላር በታች ነው። ዲሞክራሲ የመልካም አስተዳደር ስርዓት ነው። ለዲሞክራሲ መስፈን በርካታ መዋቅራዊ ሁኔታዎች መሟላት ያለባቸው ቢሆንም የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት መደረጀትና መንቀሳቀስ፣ ነፃና ፍትሃዊ የፖለቲካ ፉክክርና ምርጫ ፣ የዳበረ የነፃ ፕሬስና ሚዲያ መኖር፣ በሕግ የተገደበ ስልጣን ያለው ሕግ አውጭ አካል፣ መንግስትና ከፖለቲካ ነፃ የሆነ የፍርድና የፍትህ ስርዓት መስፈን ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የኢህአዴግ መንግስት ስለ ሰላም፣ ልማትና መልካም አስተዳደር የሚያወራው ከልቡ ቢሆን ኖሮ ኤች አር 2003 ረቂቅ ሕግ ፈጽሞ እንደዚያ ሊያስፈራውና ሊያባንነው ባልቻለ ነበር። እንደተነገረን ረቂቅ ሕጉ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚደፍር ከሆነ የኢህአዴግ መንግስት የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቀው የውጭ ድርጅት /DLA Piper/ በመቅጠር ነው ማለት ነው።

ስለ ኤች አር 2003 ብዙ ተብሏልም፣ ተጽፏልም። ረቂቅ ሕጉ ዘጠኝ ክፍሎች አሉት። በክፍል 4 ውስጥ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ስለመርዳት በሚል ርዕስ ስር የሰብዓዊ መብት ተንከባካቢ ድርጅቶች፣ የፍርድ ቤት ገለልተኛነትና ነፃነት፣ የመገናኛ ብዙኃን ነፃነትን የሚመለከት ሲሆን፣ በክፍል 5 ውስጥ ደግሞ የዲሞክራሲን ግንባታ ስለ መደገፍ በተመለከተ የዲሞክራሲን ግንባታ አስመልክቶ በአገራችን ዲሞክራሲን ለማበልጸግ ለገዢው ፓርቲና ለተቃዋሚ ድርጅቶች የሚደረግ ድጋፍን የሚመለከት ነው። እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት ምዕራፍ 3 ላይ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ስር በክፍል 1 ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት ከተዘረዘሩት አንቀጾችና በዚሁ ምዕራፍ በክፍል 2 ውስጥ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በሚመለከት ከቀመጡት አንቀጾች ጋር በምንም ዓይነት የሚጋጭ የአመለካከት ልዩነት የለውም። ረቂቅ ሕጉ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣

ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሰፍንና የአገርቱን የልማት እንቅስቃሴ ለማገዝ የአሜሪካ መንግስት አስፈላጊ የሆነውን እገዛ እንደሚያደርግ፣ ኢትዮጵያ የኢህአዴግ መንግስት እንደሚለው በማስፈጸም በኩል ያለባትን ችግሮች ለማስወገድ ይቻል ዘንድ የስልጠና እገዛ እንደሚያደርግና ረቂቅ ሕጉም ሕግ ሆኖ ሲወጣ ሕጉን ለማስፈጸም የሚያስችል ዓመታዊ በጀቱንና የሕጉን ዓላማ በግልጽ አስፍሯል።

እንግዲህ ጥያቄው የኢህአዴግ መንግስት ረቂቅ ሕጉን እንደዚያ ለምን ፈራው የሚል ይሆናል። ችግሩ ያለው ረቂቅ ሕጉ ውስጥ ተጠያቂነትን በሚመለከት በባለስልጣናት ላይ የሚጥለው እገዳ (Restriction) ላይ ነው። ስልጣን ያለተጠያቂነት ሊኖር አይችልም። ተጠያቂነትን ያለመዱ ባለስልጣናት ደግሞ ተጠያቂነትን አጥብቀው ይፈራሉ፣ ይጠላሉ። ረቂቅ ሕጉ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብዓዊ መብቶችን የጣሱ ከኢትዮጵያ ውጭ በአሜሪካና በሌሎች አገሮች ውስጥ የሚኖሩ የመንግስቱ ኃ/ማሪያም ስርዓትና የኢህአዴግ ባለስልጣናት ለፍርድ የሚቀርቡበት ሁኔታ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር እንዲያፈላልግ፣ የአሜሪካ መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን፣ ዲሞክራሲን፣ የፍርድ ቤቶችን ነፃነት፣ የመገናኛ ብዙኃን ነፃነት፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማጎልበት የሚሰጠውን የቴክኒካል ድጋፍ የኢህአዴግ መንግስት የሚያደናቅፍ ከሆነ የአሜሪካ መንግስት የሚሰጠውን ዕርዳታ እንዲያቆም ይጠይቃል። ይህ ደግሞ የደህንነት ትብብር መቋረጥን (Limitation on Security assistance) ይጨምራል። በተጨማሪም ከምርጫ በኃላ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የኃይል እርምጃ እንዲወሰድ ትዕዛዝ በመስጠት የተሳተፉና በሰብዓዊ መብቶች ረገጣ የሚወነጀሉ የኢህአዴግ መንግስት ባለስልጣናት ላይ የጉዞ እገዳ (Travel Restrictions) ይጥላል። እነዚህ ገደቦችና እገዳዎች እንቅልፍ የሚነሱትና የሚያስጨንቁት የኢህአዴግ መንግስት ባለስልጣናት እንጂ ሕዝቡን አይደለም። የጋምቤላ ክልል አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ ኦሞት ኦባንግ ኦሉም ጋምቤላ ውስጥ በአኝዋክ ተውላጆች ላይ በተፈጸመው የዘር ማጥፋት (Genocide) ተሳትፈዋል ይባላል። እኚሁ ባለስልጣን ሰሞኑን ለስራ ጉብኝት በሰሜን አሜሪካን ውስጥ ይገኛሉ። ኤች አር 2003 ረቂቅ ሕግ በአሁኑ ሰዓት ሕግ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ባለስልጣኑ ዛሬ አሜሪካ ውስጥ እስር ላይ በተገኙ ነበር። የካናዳ ባለስልጣናት አቶ ኦሞት ኦባንግ ካናዳ እንዳይቡ ቪዛ ከልክሏቸዋል። አንድ ጥያቄ ልጠይቆት። ይህ ዜና እርሶን ይረብሾታል ? መልሱን ለራስዎና ለህሊናዎ እተወዋለው።

ጥያቄው ለእኔ የኤች አር ረቂቅ ሕግ፣ ሕግ ሆኖ መውጣት አለመውጣት አይደለም። ጥያቄው በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚባለው የሕግ የበላይነት የተከበረ ከሆነ ለምንድነው አጣሪው ኮምሽን ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ባቀረበው ሪፖርት ላይ እንደገለጸው በደህንነት ኃይሎች ጭንቅላት ጭንቅላታቸውን እየተመቱ ለተገደሉ 193 ዜጎች ተጠያቂ የሚሆን አንድም የመንግስት ባለስልጣን ሊኖር ያልቻለው ? ለምንድነው ጋምቤላ ውስጥ በአኝዋክ ተወላጆች ላይ ለተፈጸመ የዘር ማጥፋት ተጠያቂ የማይኖረው ? ማነው በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያዊያን ሶማሌዎች ላይ ኦጋዴን ውስጥ ለሚፈጸመው ግድያ፣ መፈናቀል፣ መከራና ስቃይ ተጠያቂ የሚሆነው ? ይህ ረቂቅ ሕግ ወደፊት ሕግ ሆኖ ይውጣም፣ አይውጣ የኢህአዴግ መንግስት የውክልና ጦርነት ውስጥ የገባለት አገር የታችኛው ም/ቤት (Congress) ረቂቅ ሕጉን አሳልፎ ሕግ እንዲሆንለት ወደ ላይኛው ም/ቤት (Senate) መላኩ በራሱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብዓዊ መብት አያያዝና የዲሞክራሲ ሂደት ላይ ችግሮች መኖራቸውን እና ፈጽሞ ተቀባይነት የሚባል ነገር ያለመኖሩን የሚመሰክር በመሆኑ በኢህአዴግ መንግስት ላይ የተደረገ እርግማንና ውግዘት አድርገን ልናየው እንችላለን።

## የኢህአዴግና የሱዳን መንግስታት ሚስጥራዊ ስምምነት

በኢትዮጵያና በሱዳን መንግስታት መሓከል አጨቃጫቂ የድንበር ጉዳይ ኢህአዴግ ስልጣን ከመያዙም በፊት የነበር ጉዳይ ነው። ሆኖም ግን ከኢህአዴግ በፊት የነበሩት መንግስታት የድንበር ጉዳይን በተመለከተ ከሱዳን መንግስት ጋር ሚስጥራዊ ድርድር አድርገው አያውቁም። ኢህአዴግ ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከተወካዮች ም/ቤት እውቅና ውጭ ከሱዳን መንግስት ጋር በሚስጥር በመደራደር ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ያለውን 1600 ኪሎ ሜትር የሚጠጋውን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ መስጠቱን ሰምተናል። አሳልፎ በሰጠውም መሬት ላይ የሱዳን ወታደሮች እንዲሰፍሩና ኢትዮጵያዊያኖች እንዲፈናቀሉም ተደርጓል። በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ዋና ዲፕሎማት የሆኑት ሚኒስተር ሙሉ 28 ገበሬዎች መታሰራቸውንና ይፈቱልን እየተባለ እየተጠየቀ እንደነበር ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ በወቅቱ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ አድምጠናል።

እ.ኤ.አ 2004 ዓ.ም ኢህአዴግና የሱዳን መንግስት ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ያለውን 1600 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ድንበር ለማካለል በሚስጥር ተስማሙ። በስምምነቱ መሰረት የኢትዮ-ሱዳን የጋራ የድንበር ልማት ኮምሽን ተቋቋመ ። በኮምሽኑ መጠሪያ ላይ ሆን ተብሎ "ልማት" የሚል የማደናገሪያ ቃል እንዲጨመር ተደረገ። የድንበር ኮምሽኑ ዋነኛ ጉዳይ ድንበር ማካለል ቢሆንም በመጠሪያው ላይ ልማት የሚል ቃል እንዲገባ በማድረግ በሁለቱ ሃገሮች መካከል በግብርና፣ በንግድ፣ በደህንነት፣ በጤና፣ በባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት እያካሄደ የድንበሩ ጉዳይ በተለይም ከኢትዮጵያ ሕዝብ

አይንና ጆሮ እንዲርቅ ለማድረግ የሚጠቅም ታክቲክ ተደርጎ ተወሰደ። በሱዳን በኩል ተጠቃሚው የሱዳን መንግስት በመሆኑ ኮምሽኑ በየኮንፈረንሱ የሚወያይባቸ አጀንዳዎች ብቻ ሳይሆን የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሳይቀሩ በዜና መልኩ ለሕዝቡ ጆሮ ይደርሱ ነበር። በዚህ በኩል የሱዳን ትሪቡን በዋነኝነት ሊጠቀስ ይችላል። በእርግጥ የኢህአዴግን መንግስት ከድንበር ጉዳይ ይበልጥ የድንበር አካባቢ የደህንነት ጉዳይ (የተቃዋሚዎቹ የትጥቅ ትግል) ስለሚያሳስበው ከሱዳን መንግስት በኩል የደህንነት ዋስትናና ትብብር ማግኘት ፈልጓል። የሱዳን መንግስትም የኢህአዴግን ስጋት በሚገባ ስለሚያውቅ በእጁ ላይ ያለውን ካርድ በሚገባ ተጠቅሞበታል ማለት እንችላለን።

ኢህአዴግ የሱዳን መንግስትን ፍላጎት በማርካት በሱዳን ድንበር አካባቢ በመንቀሳቀስ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ የተቃዋሚ ኃይሎችን ለማጥፋት የሱዳን መንግስትን ድጋፍ ማግኘት ችሏል። ጁላይ 29 ቀን 2004 ዓ.ም የኢትዮጵያና የሱዳን የጋራ ጦር በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ከሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ተዋግተው 80 ሚሊሺያዎችን መግደላቸውን እና 80 ሚሊሺያዎችን መማረካቸውን ብርጋዴር ጀኔራል ስዩም ሓጎስ ባደረጉት ገለጻ ላይ ይፋ አድርገው ነበር። ማርች 8 ቀን 2006 ዓ.ም የድንበር ኮምሽኑ 8ኛው ኮንፈረንስ ባህር ዳር ከተማ ላይ ተካሄደ። ኢህአዴግና የሱዳን መንግስት በድንበር ጉዳይ ላይ የመግባቢያ ሠነድ ተፈራረሙ። የመግባቢያ ሰነዱ በተፈረመ በሳምንቱ በድንበር አካባቢ ነዋሪ በሆኑ የኢትዮጵያና የሱዳን ገበሬዎች መሃከል ግጭት ተነሳ። ከጎናቸው የሚቆምላቸው ያጡት የኢትዮጵያ ገበሬዎች ናቸው እንጂ የሱዳን ገበሬዎችማ ጆሮ የሚሰጥ መንግስት አላቸው። ማርች 14 ቀን 2006 ዓ.ም የሱዳን ፕሬዚዳንት ኦማር አል ባሽር በድንበር አካባቢ በኢትዮጵያና በሱዳን ገበሬዎች መሃከል የተፈጠረውን ግጭት ከኢህአዴግ መንግስት ጋር በመተባበር ለማርገብ የሚጥሩ መሆኑን ለአካባቢው አስተዳዳሪና የገበሬዎቹ ተወካዮች አረጋገጡላቸው። የኢትዮጵያ የዜና አገልግሎት (ኢዜአ) የድንበር ኮምሽኑን ኮንፈረንስ አስመልክቶ ሲዘግብ "<u>የኢትዮ-ሱዳን የጋራ የልማት ኮምሽን</u>" ባህር ዳር ከተማ ላይ ደህንነት፣ ግብርና እና የድንበር አካባቢ ንግድ በተመለከተ ውይይት አካሂዶ በጋራ ለመስራት ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ዘገበ። ኢዜአ ሰለ ኮምሽኑ ሲዘግብ ድንበር የሚለውን ቃል ከኮምሽኑ የመጠሪያ ስም ማውጣት ብቻ ሳይሆን የኮምሽኑ ዋነኛ ተግባር የጋር ልማት እንደሆነ አድርጎ ነበር ለሕዝቡ ዜና ሲያቀርብ የነበረው።

ጃንዋሪ 15 ቀን 2007 ዓ.ም የድንበር ኮምሽኑ 9ኛው ኮንፈረንስ ሱዳን ውስጥ ተካሄደ። በዚህ ኮንፈረንስ ላይ ኮምሽኑ ሁለቱ መንግስታት በድንበር አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎቻቸውን በጋራ ለማጥቃት ስምምነት ላይ ደረሱ። አፕሪል 11 ቀን 2007 ዓ.ም የሱዳን መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ የኢህአዴግ መንግስት ተቃዋሚ የሆኑ ኃይሎች በድንበር አካባቢ የሚንቀሳቀሱ መሆኑን በግልጽ በአደባባይ ላይ ይፋ አደረገ። ኦክቶበር 18 ቀን 2007 ዓ.ም 10ኛው የድንበር ኮምሽኑ ኮንፈረንስ በጋምቤላ ከተማ ላይ ተካሄደ። ኢዜአ በዚህ ኮንፈረንስ ላይ የባህል፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት የተካሄደ መሆኑን በተለመደው ቋንቋ ዘጋበ። ኢዜአ ከቀንና ከሰዓት ውጭ እውነት እንደማያወራ ቄስ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሕጻናት ሳይቀሩ ያውቃሉ። 11ኛው የድንበር ኮምሽኑ ኮንፈረንስ ዳማዚን ከተማ ላይ ሱዳን ውስጥ ተካሄደ። ኦክቶበር 22 ቀን 2007 ዓ.ም ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ የሱዳን ፕሬዚዳንት የቅርብ አማካሪ ከሆኑት ሃፊ አሊናፊ ጋር ውይይት አካሄዱ። እንደ ኢዜአ አባባል ከሆነ ውይይቱ ያተኮረው የሱዳን መንግስትና የደቡብ ሱዳን ሕዝብ ነጻ አውጪ ንቅናቄ የፈረሙትን የሰላም ስምምነት ተግባራዊነትን የተመለከተ እንደነበር ተዘግቧል። ይህን ዜና ገልብጠን የድንበር ኮምሽኑ የደረሰበትን ስምምነት ተግባራዊነት የተመለከተ ውይይት ነበር ብለን ልናነበው እንችላላን። ያለምክኒያት አይደለም ዜናውን ገልብጠን እናንብበው ያልኩት። ኖቬምበር 18 ቀን 2007 ዓ.ም የድንበር ኮምሽኑ በካርቱም የፖሊስ ክለብ ውስጥ ለ7 ተከታታይ ቀናት ስብሰባ አካሂዶ ከሁለቱም ወገኖች የተወጣጣ የጋራ ቡድን ተቋቁሞ በድንበር አካባቢ ጉብኝት አካሄደ። ጠ/ሚሩ ስለ ድንበር ኮምሽኑ ም/ቤት ውስጥ ኢትዮጵያ ለሱዳን መሬት አለመስጠትዋን እና የተፈናቀለ አንድም ገበሬ እንደሌለ ተናግረዋል። ከአሁን በኃላ የሚናገሩት አዲስ ነገር ይኖራል ብሎ የሚጠብቅ ሰው ያለ አይመስለኝም። ጀርመኖች ሁሉንም የተናገረ፣ መጨረሻ ለይ የሚናገረው የለውም (Wer alles sagt, sagt am ende gar nichts) ይላሉ። ሆኖም ግን በውጭ የሚኖሩ የኢህአዴግ መንግስት ደጋፊዎች ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ድንበር አሳልፎ ለሱዳን በመስጠት ኢትዮጵያ የምታገኘው ጥቅም ምንድነው ብለው ከሁሉም በላይ በመጀመሪያ ይሰማቸው እንደሆን ኢህአዴግን ቀጥሎም በጣም ቅርባቸው ለሆነው ህሊናቸው ጥያቄ ሊያቀርቡ ይገባል ብዬ አምናለሁ።

## *መደምደሚያ*

አመኔታ ለፖለቲከኛ ዋና ካፒታሉ ነው የሚል አባባል አለ። ብሔራዊ ጥቅም ምንጩ ብሔራዊ ማንነት ነው። በብሔራዊ ጥቅምና በሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ በዜጎችና በመንግስት መሓከል ልዩነት ሊኖር አይችልም። ኢህአዴግ በሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ የሕዝብ አመኔታ የሌለው መንግስት ነው። የኢህአዴግ ባለስልጣናትም ሲዋሹ ሕዝቡ ይታዘበናል ብለው የሚፈሩ እንኳን አይደሉም። መቼስ እኛ ኢትዮጵያዊያን

እንደ ናይጄሪያዊያን ወንድሞቻችን በስነ ጹሑፉ ዓለም ለኖብል ሽልማት (Nobel Prize) የበቃ የስነ ጽሑፍ ሰው ማፍራት ባንችልም የፖለቲካ፣ የማዕበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮቻችንና ብሶታችንን አስመልክቶ በቀልድ፣ በግጥም፣ በዘፈን መልኩ በማቅረብ የአፍ ስነ ጹሑፍ (Oral Litreature) እና በተለይም በፖለቲካ አሽሙር (Political Satire) በአፍሪካ ውስጥ ሊስተካከለን የሚችል ያለ አይመስለኝም። ከአገር ቤት ከመጣ ሰው የሰማሁት ቀልድ ነው። አንድ ውጭ አገር የቆየ ሰው አዛውንት እናቱን ለመጠየቅ ወደ ኢትዮጵያ ይመጣል። ጎረቤት እየሄዱ ቴሌቪዥን ማየት ለሚወዱት እናቱ ትልቅ ቴሌቪዥን ከነማስቀመጫው ገዝቶላቸው የዕረፍት ጊዜውን ጨርሶ ወደ መጣበት አገር ይመለሳል። ተመልሶ ከአንድ ዓመት በኃላ እናቱን ለመጠየቅ ይመጣል። ቤት ውስጥ ባየው ነገር በጣም ይገረምና ራሱን ይጠይቃል። ትልቁ የቴሌቪዥን ማስቀማጫ ላይ ሚጢጢ ቴሌቪዥን ተቀምጣለች። ልጅ ሲፈራ ሲቸር እናቱን:- ”ባለፈው የመጣሁ ጊዜ ትልቅ ቴሌቪዥን አልነበረም እንዴ የገዛሁልሽ፣ ምንድነው እንደዚህ ያሳነሰው?” ሲል ይጠይቃል። እናትም:- “ልጄ ምን ይደረግ ብለህ ነው ኢህአዴግ ነጋ ጠባ ሲዋሽ ቴሌቪዥኔ ሲሸማቀቅ፣ ኢህአዴግ ሲዋሽ ቴሌቪዥኔ ሲሸማቀቅ፣ ሲሸማቀቅ አንሶ ነው እንደዚህ ትንሽ የሆነው አሉት።“ ይባላል። እኔን በግሌ በጣም የሚያስደነግጠኝ ነገር ቢኖር ግን የኢህአዴግ ውሸት ሳይሆን አንዳንድ የኢህአዴግ ባለስልጣናት ለሕዝብ ያላቸው ንቀት እና ለሰው ህይወት የሚሰጡት ግምትና የሚታይባቸው ጭካኔ ነው። እነዚህ የኢህአዴግ ባለስልጣናት በደም ስራቸው ውስጥ ደም ሳይሆን ቀዝቃዛ ውሃ የሚዘዋወረ ነው የሚመስለኝ።

እንግዲህ የሚያሳዝነው የሉዓላዊነት ጉዳይ በሕገ መንግስቱ እንደተደነገገው የሕዝብና የመንግስት ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ አንድ ድርጅት ማለትም ኢህአዴግ ብቻውን እንዳሻው የሚያዝበት ጉዳይ መሆኑ ነው። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የኢህአዴግ መንግስት ሲልን የነበረው ወደ ጦርነት የገባነው ሉዓላዊነታችን ስለተደፈረ ሲሆን ሻዕቢያን ከድንበራችን ካስወጣን በኃላ ሌላ አጀንዳ አይኖረንም የሚል ነበር። ታዲያ ሶማሊያ መች ነው የኢትዮጵያን ድንበር የደፈረችው ብሎ ለሚጠይቅ መልስ ያለ አይመስለኝም። የሶማሊያ ጦርነት የራሱ የሆነ ስጀንዳ ያለው በመሆኑ ሕዝቡም፣ በምክር ቤት ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎችም ድጋፍ የነሱት ያለ ምክኒያት አይደለም። የአልጀርሱም የሰላም ስምምነትም ኢትዮጵያን የሚጫን፣ የግዛት ሉዓላዊነቷን የማያስከብር፣ ኢትዮጵያን የሞተና የተቀበረ የቕኝ ገዢ ሠነዶችን እንድትቀበል ያስገደደ ውል ነበር። በባድመ ጉዳይ የስትራቴጂና የስልት ጥያቄዎች በሚል በጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ጁላይ 2003 ዓ.ም ተዘጋጅቶ የነበረው ሚስጥራዊ ሰነድ ገጽ ሶስት ላይ: “… ትግላችን የሕግና የሰላም እንጂ የመሬት ወይም የወደብ አይደለም። ሰላም ካገኘን ባለንበት ሆነን ተአምረኛ ልማት ልናስመዘግብ፣ ማንኛውም መሬት ሊሰጠን ከሚችለው በእጅጉ የላቀ ጥቅም ልናገኝ እንችላለን። ሰላም ከሌለ ደግሞ ደርግ አሰብን ይዞ አገሪቱን ወደ መቀመቅ እንደከተተው ሁሉ እኛም ወደዚያው እናመራለን። ስለዚህ በህግና በሰላማዊ መንገድ ለሄደ መሬት ብለን አንዋጋም። …” ይላል። ይህ እንግዲህ ባድመ አንዴ ሄዷል የራሱ ጉዳይ የሚል አንደምታ አለው። ባድመ ላይ የሚኖሩ ወገኖቻችን የዜግነት ጉዳይ ምን ይሆናል ለሚለው ጥያቄ ግድ ያለው ባለስልጣን ያለም አይመስለኝም። ለሱዳን በተሰጠውም መሬት ላይ የሚያርሱ ገበሬዎች አይፈናቀሉም ተባለ እንጂ የዜግነት እጣ ፈንታቸው ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ ኢህአዴግን ቅንጣት ያህል እንኳን የሚያስጨንቀው ጉዳይ አይመስለኝም። በሉዓላዊነት ትርጉም ላይ በኢህአዴግና በሕዝቡ መሓከል ትልቅ ልዩነት አለ። በመሆኑም ለኢህአዴግ መንግስት የሉዓላዊነት ጉዳይ የስልጣን ጉዳይ ብቻ ነው።